# ተዓምረኛው አባይ

**ሰንደቁ ገረመው**

12-23-14

የአባይ ወንዝ ታሪክ ዳግም በማይመለስበት ሁኔታ ተለውጧል፡፡ አባይ የዓለማችን ረዥሙ ወንዝ መፍለቂያ ማህፀኑ ኢትዮጵያ ሆና ሀገራትን በማቋራረጥ አዳርሶ ሲያበቃ ከረዥሙ ጉዞው የሚገላገለው ሜዴትሬንያን ባህር ሲገባ ነው፡፡ አባይ የወንዞች ሁሉ ታላቅና ንጉስ ሲሆን ፈለገ ግዮን በሚል ስምም ይጠራል፡፡ በአብዛኛው አባይ እንለዋለን፡፡ አባይ ታላቁ የተፈጥሮ ፀጋና ስጦታችን ሲሆን ሳንጠቀምበት ሳይጠቅመን እኛ እየተራብን ሌሎችን ሲያጠግብ ኖሯል፡፡ ይኼ ቁጭትና መነሳሳት ደግሞ የአባይን ታሪክ እንደገና ለመጻፍ እንደገና በአዲስ መልክ ለመሥራት አብቅቶናል፡፡

ትናንት አባይ ወንዝ ነበር፡፡ ትንሽ ቆይቶም 240 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ታላቅ ውኃ የተኛበት ከባህርም በላይ መርከቦች የሚንፈላሰሱበት ከውቅያኖስ መለስ ያለ ታላቅ ባህር ይፈጥራል፡፡ ይሆናል፡፡ አባይን በማንም የውጪ እርዳታና እጅ ሳይሆን በራስ አቅም ብቻ ለመሥራት በመወሰን የማይደፈረውን ለደፈሩት እጅግ ቆራጦች የላቀውና የመጨረሻው ምሥጋና ይገባቸዋል፡፡

ብዙዎች በንቀት ድሆች ስለሆኑ እንኳን በአባይ ላይ ታላቅ ግድብ ለመገንባት ቀርቶ ራሳቸውን በምግብ ያልቻሉ ድሆችና ረሀብተኞች ናቸው ሲሉ ተሳልቀውብናል፡፡ ጊዜና ዘመን ባለመፍቀዱም አባይን ገድቦ ለኢትዮጵያ ጥቅም ለማዋል በምንም ዓይነት መንገድ የማይሞከር፣ የማይታሰብና የማይቻል የማይገመትም ነበር፡፡ የመገደቡን ሀሳብ ለመከላከል ግብፆች ረዥም ዘመናት ታግለውናል፡፡

ከየትኛውም ዓለም አቀፍ የእርዳታና የብድር ተቋማት ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት እገዛ እንዳታገኝ፣ አቅም አግኝታ እንዳትገነባ ይህ ቀረሽ የማይባል ዘመን የማይሽረው ለብዙ ዓመታት የኖረና የዘለቀ ከጥንት ካሊፋይቶች እስከዛሬዎቹ መሪዎች ድረስ እየተቀባበሉ በብዙ መልኩ ሲተናነቁን ኖረዋል፡፡

በዚህም የውጭና የውስጥ ችግሮች መንስዔነት 85 ከመቶ የአባይ ውኃ አመንጭና ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ በአባይ ውኃ ሳትጠቀምና ማግኘት ያለባትን ጥቅም ሳታገኝ ኖራለች፡፡

ጊዜ ፈቅዶ የማንንም የውጪ እርዳታ ሳትፈልግ በራሷ ሕዝብና ሀገራዊ አቅም ለመሥራት ቆርጣና ታጥቃ ስትነሳ ይህንንም ለማሰናከል ይህ ቀረሽ የማይባል ጫጫታና እሪታ ከግብፆች ወገን ተሰምቷል፡፡

ፖለቲካኞችና መሪዎችም እስቲ ሲሰራ እናያለን የሚል ዛቻና ቀረርቶ ሲያሰሙ ቆይተዋል፡፡ በአባይ ውኃ ለም አፈራችንና የማዕድን ሀብታችን ታጥቦ እየተወሰደ እኛ በድህነትና በልመና ስንኖር ግብፆች ደግሞ በሀብትና በጌትነት ኖረዋል፡፡ እነሆ አሁን የአባይ ታሪክ ሙሉ በሙሉ እየተቀየረ ይገኛል፡፡

ይህን ሁኔታ ለመለወጥ ኢትዮጵያ በራስዋ አቅም የአባይን ግድብ ለመሥራት ወስና ስትንቀሳቀስ እነዚሁ ወገኖች የተለያዩ ፈተናዎችን በመጋረጥ ከራሳቸውም ሀገር አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃም ተንቀሳቅሰዋል፡፡

ኢትዮጵያ የአባይ ውኃ 85 ከመቶ ባለቤት ብትሆንም ይህንን የተፈጥሮ ፀጋ ብቻዬን ልጠቀምበት አላለችም፡፡ አባይ ተጋሪ ለሆኑት ሀገሮች በሙሉ ይበቃል፡፡ በሚገነባው ግድብ ግብፅ ማግኘት የሚገባትን ውኃ ታገኛለች፡፡ የሚቀንስባት የለም፡፡ ሌሎችም እንዲሁ፡፡

ኢትዮጵያ የአባይን ውኃ ለሀገሯ ልማት የመጠቀም መብት አላት፡፡ የሚገነባው ታላቁ የህዳሴ ግድብ የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጭ በመሆኑ ጠቀሜታው ለጐረቤት ሀገሮችም እድገት ጭምር ነው፡፡

ኢትዮጵያ ግብፆች ሥጋታቸውን ትተው በጋራና በመመካከር የጋራ ተጠቃሚ በሚያደርገን ጉዳይ ልንመክርና መግባባት ላይ መድረስ አለብን የሚለውን አቋሟን በተደጋጋሚ ገልፃለች፡፡ ተቋርጦ የነበረው የሦስትዮሽ ውይይት (በኢትዮጵያ፣ በግብፅና ሱዳን) መካከል እንዲቀጥል መደረጉም የተሻለ ተስፋን ፈንጥቋል፡፡

ኢትዮጵያ የታላቁን ሕዳሴ ግድብ ግንባታ እጅግ በተጠናከረ ሁኔታ አጠናክራ በመቀጠሏ አሁን 42 በመቶ ሥራው ተገባዷል፡፡ ይህ እጅግ አስደናቂና አስገራሚ

የግድብ ግንባታ ኢትዮጵያን በአፍሪካ የመጀመሪያና ቀዳሚ ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት የኃይል ማመንጫ ያላት ሀገር ያደርጋታል፡፡

የግድቡ ሥራ በሁሉም ኢትዮጵያዊ የገንዘብ መዋጮና ባለቤትነት የሚካሄድ ከመሆኑም ሌላ በግድቡ ሥራ ላይ የተሰማራው በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሆነውና በኢትዮጵያ ረዥም ዘመን በኖረው የጣልያኑ ሣሊኒ ካምፓኒ አማካሪነትና ግንባታ የሚሰራ በመሆኑ በተለያየ መስክ ተሰማርተው የሚሰሩ ኢትዮጵያውን በመሀንዲስነት ኤሌክትሪካል ኢንጂነርነት በቀያሽነት በማሽን ኦፕሬተርነት ወዘተ ሰፊ በተግባር የታገዘ የእውቀት ሀብት እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡

ይህም ለቀጣይ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ግንባታ ሰፊ እውቀትና ልምድን የሚሰጥ የበለጠም ሥራ እንዲከውኑ ብቁ ያደርጋቸዋል፡፡ የታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ በሚካሄድበት ሥፍራ ሥራዎች በፈረቃ የሚሰሩ ሲሆን አንዲትም የምትባክን ሴኮንድ የለችም፡፡ ጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ሌትና ቀን ሳይሉ የበረሀው ሐሩር ሳይበግራቸው ሥራቸውን ሁሉ በታላቅ ሕዝባዊና ሀገራዊ ወኔ እየከወኑ ይገኛሉ፤ ከልብም ያኮራሉ፡፡

የግድቡ ሙሌት ወደሥር አለቱ ተፈልፍሎ ማመን በማይቻልበት ሁኔታ የጠለቀና ፍፁም አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ የተገነባ ሲሆን ዛሬ ከፍታው 570 ሜትር ላይ ደርሷል፡፡ የተወሰነለት ከፍታ ላይ ሲደርስ ያበቃል ተብሎ ይገመታል፡፡ ከወዲያ ማዶና ከወዲህ ባሉ በተራራቁ ተራሮች መሀል የሚካሄደው የግንባታ ሥራ በስተመጨረሻ ተራሮቹን በአንድ ቀጥተኛ መስመር ያገናኛቸዋል፡፡ ድንቅና ታላቅ ጥበብ የተገለጠበት የኢትዮጵያውያን ሥራ ነው፡፡ እፁብ ድንቅም ያሰኛል፡፡

የተጠለፈውም የአባይ ውኃ መስመሩን ጠብቆ በከፍተኛ ግርማ ሞገስ እያስገመገመ ሲያልፍ ከግድቡ ላይ ሆኖ ማየትም ይቻላል፡፡ ውኃው የሚፈለገው ቦታ ከደረሰ በኋላ በውስጡ በማለፍ ፍሰቱን ወደሱዳንና ግብፅ ይቀጥላል፡፡ ይህም የአባይ ውኃ ፍሰት ይቀንሳል ለሚሉት ግብፆች ውኃው እንደማይቀንስ የግብፅ አምባሣደር በቦታው ተገኝተው መመልከት ችለዋል፡፡

የአባይ ግድብ ሌላው አስገራሚ ተዓምራት ውኃው በ240 ኪሎ ሜትር ተራሮች ሸጦች ሜዳዎች ላይ የሚያርፍ መሆኑ ነው፡፡ ለዚህም የደን ምንጣሮው ሥራ

በስፋት እየተካሄደ ውኃውን ሊበክሉ የሚችሉ የእፅዋት ዝርያዎች እንዲወገዱ እየተደረገ ነው፤ የእፅዋት ዘሮቹም እንዳይጠፉ ናሙናቸው በየዓይነቱ በባለሙያዎቹ ተጠንቶና ተለይቶ በእፅዋት ዘር ባንክ ውስጥ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

ከአባይ ግድብ ጀርባ 240 ኪሎ ሜትር መሬት ላይ የሚተኛው ውኃ ራሱን ችሎ ብዙ ተዓምራትን ይፈጥራል፡፡ 240 ኪሎ ሜትር ርቀቱ ከአዲስ አበባ እስከ አዋሻ ድረስ ማለት ነው፤ ውኃው በምን ያህል ሰፊ ግዛት ላይ እንደሚተኛ ማንም ሰው በዓይነ ሕሊናው ሊገምተው ይችላል፡፡ ግድቡ ሲጠናቀቅ ውኃው ተገቢውን ቦታ ሁሉ ሞልቶ እንዲይዝ ለማድረግ ወይንም እስኪሞላ ጥቂት ጊዜ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

በሌላም መልኩ ውኃው ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዳይሄድ በተለያዩ ቦታዎች የማገድ ግንባታዎችም ከወዲሁ መሥራትም ይጠይቃል፡፡ ውኃው ሞልቶ እንዳይፈስም በተለያዩ ቦታዎች ማስተንፈሻዎች አሉት፡፡

እነዚህ በተሟላ ሁኔታ ተሰርተው ሲጠናቀቁ የአባይ ውኃ የአባይ ግድብ ወንዝ መሆኑ ይቀርና 240 ኪሎ ሜትር ውኃ የተኛበት በዓይነቱም አቻና ግጥም የሌለው ታላቅ ባሕር ወይንም መለስተኛ ውቅያኖስን ፈጠርን ማለት ነው፡፡ አንዳንዶች የሚተኛውን ውኃ የጣናን ሐይቅ ሁለት እጥፍ ይሆናል ቢሉም ከጣና ሐይቅ በብዙ እጥፍ የሚበልጥ ጭርሱንም የማይገናኝ መለስተኛ ውቅያኖስ እንደሚፈጠር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

ይህ የአባይ ግድብ ግንባታ ተጠናቆ ውኃው ቦታውን ሲይዝ በ240 ኪሎ ሜትር ክልል ውስጥ የሚንቀሳቀሱ አነስተኛና መካከለኛ መርከቦች ይኖሩታል ማለት ነው፡፡ በብዙ አቅጣጫ የሚገኙ የተለያዩ ደሴቶችምይፈጠራሉ፡፡ ከፍተኛና የማያቋርጥ የቱሪስት ጐብኝዎችን ዓይንና ትኩረት በመሳብ የቱሪስት ገቢያችንን ሊታመንና ሊገመት ከሚችለው በላይ ያሳድገዋል፡፡

የግድቡ መኖርና የውኃው መተኛት የአካባቢውን የአየር ንብረት ሚዛን በመለወጥ በረሀማ የነበረውን ሥፍራ በደኖችና በተክሎች በመሸፈን ፍፁም አረንጓዴ በመሆን ተመራጭ ሥፍራ ያደርገዋል፡፡ በእርግጥኝነት ብዙ ደሴቶች ይኖሩናል፡፡ ይህም የሆቴል ኢንቨስትመንትን በላቀና ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዲያድግና እንዲስፋፋ ያደርገዋል፡፡

በተለያዩ ከግድቡ በርቀት በሚገኙ ሥፍራዎች መለስተኛ የአውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያዎች መሥራት ግድ ይሆናል፡፡ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ቱሪስቶች የጉብኝት ማመላለሻ ይረዳል፡፡

ይህንኑ ድንቅና ተዓምረኛ የታላቁን ሕዳሴ ግድብ ግንባታ እንደ ጀመርነው በታላቅ ሀገራዊ ወኔ ስንጨርሰው በሚፈጠሩት የተለያዩ ሐይቆች ላይ ሰፊ የአሣ ምርት እንደ አሸን ስለሚፈላና ስለሚያጥለቀልቀው በአቅራቢያዎቹ የአሣ ምርቱን በዘመናዊ ሁኔታ የሚከውኑ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ የአሣ ምርት ዘመናዊ ፋብሪካዎች ይኖራሉ ማለት ነው፡፡

ፈጣን የባቡር አገልግሎቶችም ታሳቢ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ 240 ኪሎ ሜትር ውኃ በሚሸፍኑት የሩቅ አካባቢዎች የአባይ ገባር ወንዞች በሙሉ ወደ አባይ በሚፈሱበት የተለያየ አቅጣጫና አካባቢም የመስኖ ልማቶች ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡ የብርቱካን፣ የፓፓያ፣ የማንጎ፣ የመንደሪን ወዘተ…የአትክልት ልማቶች በሰፊው ሊካሄዱ ከመቻላቸውም በላይ ሰፋፊ ዘመናዊ የመካናይዝድ እርሻዎችም ታሳቢ ናቸው፡፡ የምግብ ዋስትና ችግር ሙሉ በሙሉ ተፈትቶ ኢትዮጵያ ከራሷ አልፎ ለሌሎች የምትተርፍበት ሁኔታም በቅርብ ዓመታት እውን ይሆናል፡፡

እነዚሁ ሁሉ የተለያዩ ሰፋፊ የሥራ መስኮች ለብዙ መቶ ሺህ ኢትዮጵያውን አዳዲስ ህይወቶችንና ሥራዎችን በእርግጠኝነት እንደሚፈጥሩ መገመት ይቻላል፡፡240 ኪሎ ሜትር የውኃው ማረፊያ ስፋት ሲሆን በአካባቢው ዘመናዊ የጀልባና የመለስተኛ መርከብ መገንቢያ ማደሻ ፋብሪካም እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡

እነዚህ እንግዲህ የአባይ ታላላቅ ትሩፋቶች ብለን ልንወስዳቸው የምንችላቸው ናቸው፡፡ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ስድስት ሺህ ሜጋ ዋት ኃይል ሲያመነጭ ለጎረቤት ሀገሮች ብቻ ሳይሆን ለሩቅ ሀገሮችም የኤሌክትሪክ ኃይል በውጭ ምንዛሪ እንድንሸጥ ያስችለናል፡፡ ይህም የሀገሪቱን ገቢና የዜጎቿን ሕይወት ደረጃ በደረጃ ሙሉ በሙሉ ይለውጠዋል ከምንለው ወጪ የግድቡን በስኬት ተሰርቶ መጠናቀቅ ተከትሎ የሚገኙ ፈርጅ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉ፡፡

ኢትዮጵያ የአባይ ግድብ ተሰርቶ ሲጠናቀቅ አሁን በመሰራትና ለፍፃሜ የደረሱትን ጨምሮ የ11 ግድቦች ባለቤት ያደርጋታል፡፡ ይህ እጅግ ታላቅና ድንቅ ሀገራዊ ሀብት የዜጎችዋ መኩሪያና መመኪያ ለቀጣዩም ትውልድ ዘመን የማይሽረው ቅርስ በመሆኑ የተጀመረው ሕዝባዊ መነሳሳትና ፕሮጀክቱን የማሳካትና አጠናክሮ የመቀጠሉ ሥራ ወደ ኋላ የሚባል አይደለም፡፡

የታላቁን ሕዳሴ ግድብ ግንባታ መሪው ፓርቲና የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሳቸው አቅም፣ እውቀትና ገንዘብ እንደመሩት ሁሉ ለፍፃሜም እንደሚያደርሱት በልበ ሙሉነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ሕዝቡን ከዚህና ከሌሎችም ታላላቅ የሀገራዊ ልማትና እድገት ሥራዎች ለማዘናጋትና ለማደናቀፍ አመፅና ሁከት ለመፍጠር የሚክለፈለፉ ተቃዋሚዎችንም ሕዝቡ አምርሮ በመታገል እርቃናቸውን እንደሚያስቀራቸው ይታመናል፡፡

ሕዝብ የሀገርን ልማትና እድገት እንጂ የጨለማ ኑሮ፣ ድህነትን፣ ተረጂነትን፣ ተመፅዋችነትን ዳግም የኋሊት ጉዞን ጭርሱንም አይፈቅድም፤ በደረሰበትና ባገኘው እድገት ላይ መጨመርን እንጂ መቀነስን አይመኝም፡፡

በኢትዮጵያዊነትና በሕዝብ ተቆርቋሪነት ስም እየነገዱና እየሸቀጡ ሕዝባዊ አመፅን በመስበክ የተሰማሩት አንዳንድ ተቃዋሚ ቡድኖች ከጭፍን የፖለቲካ ጥላቻ ያልወጡ፣ በዘረኝነት ስሜት የተጠመቁና የተለከፉ የሀገሪቱን ልማትና እድገት ሳይሆን እልህ በመጋባት በበቀል ስሜት በመነሳት ውድቀትና ጥፋትን የሚናፍቁ በመሆናቸው ጥቂት አባሎቻቸውን ይዘው ቢጮሁም መላው ሕዝብ አይሰማቸውም፡፡ ለእነሱ ሲል የሚያጠፋውም ጊዜ የለም፡፡

ይህንን ግዙፍ ሀገራዊ ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ ታላቅ የልማትና የእድገት ራዕይና ተጨባጭ ሥራ ሊያሳኩ የሚችሉበት አቅሙም ብቃቱም የላቸውም፡፡ የእነሱም የቁራ ጩኸት ሰሚ የለውም፡፡ የሀገሪቱ ልማትና የእድገት ጉዞም እንቅፋቶቹን በማለፍ በድል አድራጊነት ግስጋሴውን ይቀጥላል፡፡ የሚገታው አንዳችም ኃይል አይኖርም፡፡ አባይም ተዓምረኛነቱን ደግሞ ደጋግሞ ያሳየናል፡፡